


# 2018 ዓ.ም

## አርባምንጭ

# ይዘት

- ክፍል አንድ፡- አጠቃላይ ሁኔታ
- **1.1.** ዓላማ
- **1.2.** ወሰን
- **1.3.** ትርጓሜ
- ክፍል ሁለት፡- የታክስ ማስታወቂያዎች እና ቅጾች
- **2.1.** የታክስ አስተዳደርን በሚመለከት
- **2.2.** የገቢ ግብርን በሚመለከት

# ይዘት…

2.3. ተጨማሪ እሴት ታክስን በሚመለከት

2.4. ኤክሳይዝ ታክስን በሚመለከት

2.5. ቅጾች እና ማስታወቂያዎች

2.6. የታክስ ማስታወቂያ ዘግይቶ ማቅረብ አስተዳደራዊ ቅጣት

ማጠቃለያ

ማጠቃሻ

## 1.1. ዓላማ

- ❑ **ዋና ዓላማ**

➢ በታክስ አስተዳደር አዋጅ መሠረት በማወያየት ታክሱን በወቅቱ ለገቢ መሥሪያ ቤቱ እንዴት እንደሚያሳውቁ እና በምን እንደሚያሳውቁ ይለያሉ።

- ❑ **ዝርዝር ዓላማ**

✓ የታክስ አስተዳደርን የታክስ ማስታወቂያ አቀራረብን ያብራራሉ፤

✓ ሰነድን የማቅረቢያ ወይም ታክስ የመክፈያ ጊዜ ያብራራሉ፤

✓ ታክስን በኤሌክትሮኒክስ የታክስ ሥርዓት መጠቀም ያለውን ጥቅም ይገልጻሉ፤

✓ ታክስን ባለማሳወቅ የሚያስከትለው ቅጣት ያብራራሉ።

# 1.2. ወሰን

- **የሰነዱ ሽፋን**

- የፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008፣
- በተሻሻለዉ የፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 1395/2017፣
- የፌደራል የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009፣
- የፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008፣
- የፌደራል ታክስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 407/2008፣
- የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁ.285/1994 እና ይህን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁ.609/2008 እና አዋጅ ቁ.1157/2011፣
- የኤክሳይዝ ታክስ ለማስከፈል የወጣ አዋጅ ቁጥር 1186/2012።

# ወሰን..

- ስልጠናዉ የሚወስደዉ ጊዜ



# 1.3. ትርጓሜ



# ክፍል ሁለት:- የታክስ ማስታወቂያዎች እና ቅጾች

## 2.1. የታክስ አስተዳደርን በሚመለከት

## 2.1.1. የታክስ ማስታወቂያዎችን ስለማቅረብ

- ማስታወቂያው በባለሥልጣኑ በፀደቀው ቅጽ መሠረት መቅረብ አለበት።
- ባለሥልጣኑ በታክስ ከፋዩ ወይም በታክስ ከፋዩ ስም በቀረበ የታክስ ማስታወቂያ አይገደድም።
- ማንኛውም ታክስ ከፋይ በሚያቀርበው የታክስ ማስታወቂያ ላይ መፈረም የሚኖርበት
- ታክስ ከፋዩ የታክስ ማስታወቂያውን ለመፈረም የማይችል ግለሰብ ሲሆን የታክስ ወኪል/የታክስ እንደራሴው የታክስ ማስታወቂያውን ሊፈርም እና የማረጋገጫ መግለጫ ሊሰጥ ይችላል።

## 2.1.3. በታክስ እንደራሴዎች የሚቀርብ የታክስ ማስታወቂያዎች

- ✓ አንድ የታክስ እንደራሴ **የታክስ** ማስታወቂያ ማቅረብንና ታክስ መክፈልንም ጨምሮ የታክስ ሕግ በታክስ ከፋዩ ላይ የሚጥለውን ማንኛውም ግዴታ የመወጣት ኃላፊነት አለበት።

- ✓ **የታክስ እንደራሴ**:- ማለት ታክስ ከፋዩን በመወከል በኢትዮጵያ ውስጥ ማንኛውንም ገንዘብ ለመቀበል/ለመክፈል ኃላፊነት ያለበት ግለሰብ ሲሆን የሚከተሉትን ይጨምራል:-

- ➢ የሽርክና ማህበሩ ሽሪክ/ሥራ አስኪያጅ፣

# በታክስ እንደራሴዎች....

- የኩባንያው ዳይሬክተር፤
- ችሎታ የሌለውን ግለሰብ በመወከል ጥቅም/ገቢ የሚቀበል ህጋዊ ወኪል፣
- የአንድ ታክስ ከፋይ ሀብት ተረካቢ በተመለከተ የታክስ ከፋዩ ባለአደራ፣

## 2.1.4. የታክስ ማስታወቂያዎች አስቀድሞ ስለማቅረብ

- ሥራውን ያቋረጠ ሥራውን ካቆመበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት። ሥራውን ባቆመ በ60 ቀናት ውስጥ/ባለሥልጣኑ በሚሰጠው የጽሑፍ ማስታወቂያ በሚወስነው ከዚያ ባነሰ ጊዜ ውሰጥ:-
  - የቅድሚያ ታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ እና ሊከፈል የሚገባውን ታክስ መክፈል አለበት።
- ታክስ ከፋይ ከኢትዮጵያ ሊወጣ ከሆነና በጊዜያዊነት አለመሆኑ የሚገመት ከሆነ ከመውጣቱ በፊት:-
  - የቅድሚያ ታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ እና ታክስ መክፈል ወይም የሚከፈልበትን አኳሃን ማመቻቸት አለበት።

## ማስታወቂያዎች አስቀድሞ ስለማቅረብ...

- ❑ ታክስ ከፋዩ ማቅረብ በሚገባው ጊዜ አያቀርብም ብሎ ማመን የሚያስችል ምክንያት ሲኖር ባለሥልጣኑ የጽሑፍ ማስታወቂያ በመስጠት:-

- ➢ የቅድሚያ ታክስ ማስታወቂያ እንዲያቀርብ እና ታክስ ባለሥልጣኑ በሰጠው ማስታወቂያ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ እንዲከፍል፣ ሊያዝ ይችላል።

## ሙከራ አንድ

- ❑ የታክስ አስተዳደርን በሚመለከት የታክስ ማስታወቂያ አቀራረብን አብራሩ?

# 2.2. የገቢ ግብርን በሚመለከት

- **ከመቀጠር የሚገኝ ገቢን በሚመለከት፤**

  - አንድ ሠራተኛ ከአንድ በላይ ቀጣሪዎች ያሉት ወይም ከራስ ገቢ ላይ ግብር ቀንሶ የመያዝ ግዴታ ያለበት እንደሆነ ከየሦስት ወሩ መጨረሻ በኋላ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ የግብር ማስታወቂያ ማቅረብ ይኖርበታል።

- **ከቤት ኪራይ እና ንግድ ሥራ ገቢ ግብርን በሚመለከት፤**

አንቀጽ 89 ግብርን ስለመክፈል **ንዑስ አንቀጽ (5)፡-** በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2 እና 4 የተደነገገው ቢኖርም ለመጀመሪያ ጊዜ ዘገቢ ግብር የሚከከፍሉ አዲስ ግብር ከፋዮች የመጀመሪያውን የግብር ዓመት በተመለከተ ዓመታዊ ግብር የሚከፍሉት በሚከተለው አኳኋን ነው፡-

ሀ) የደረጃ "ሀ" አዲስ ግብር ከፋዮች ዓመታዊ ገቢያቸውን ማስታወቅ ባለባቸው ጊዜ በግብር ዓመቱ ሊከፈል የሚገባውን ግብር መክፈል አለባቸው::

ለ) የደረጃ "ለ" አዲስ ግብር ከፋዮች ከሐምሌ 1 ቀን እስከ ሐምሌ 30 ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ግብሩን መክፈል አለባቸው።

# የገቢ ግብርን በሚመለከት…

- **የሰንጠረዥ “መ”ን በሚመለከት፤**
  - ግብሩ ተቀናሽ ካልተደረገ በስተቀር የሰንጠረዥ “መ” ግብር ከፋይ ገቢውን ያስገኘው ግብይት ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሁለት ወራት፡፡
- **የቅድመ ግብርን በተመለከተ፤**
  - በሀገር ውስጥ ከሚፈጽሙ ክፍያዎች ላይ በወሩ ውስጥ ቀንሶ ቀሪ ያደረገውን አጠቃላይ ግብር ከወሩ የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ገቢ የሚደረግ ሲሆን ዕቃዎች ወደ ሀገር በሚገቡበት ጊዜ የቅድሚያ ግብር የሚከፍለው በጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች በኩል ነው፡፡

# 2.3. ተጨማሪ እሴት ታክስን በሚመለከት

የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 1341/2016

**የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ**

- ማናቸውም የተመዘገበ ሰው የእያንዳንዱን የሒሳብ ጊዜ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ የሒሳብ ጊዜው ከተጠናቀቀ በኋላ ቀጥሎ ባለው ወር የመጨረሻ ቀን ድረስ ማቅረብ አለበት።
- ማናቸውም የተመዘገበ ሰው በሒሳብ ጊዜው ውስጥ ተከፋይ የሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ ገቢ ቢኖረውም ባይኖረውም የሒሳብ ጊዜውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ የማቅረብ ግዴታ አለበት።

## 2.5. ኤክሳይዝ ታክስን በሚመለከት

- በኢትዮጵያ ውስጥ፤
  - የተመረቱት ዕቃዎች ከአምራቹ ፋብሪካ በሚወጡበት ጊዜ፤
  - ፋብሪካ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ዕቃዎች ጥቅም ላይ በዋሉበት ጊዜ፤
  - በአንድ ወር ውስጥ ከማምረቻው ፋብሪካ ወጪ ባደረጋቸው ዕቃዎች ላይ ሊከፍል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ የሚቀጥለው ወር 30ኛው ቀን ከማለፉ በፊት ለታክሱ ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ አለበት።

# ኤክሳይዝ ታክስን በሚመለከት...

- በማናቸዉም አንድ ወር የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈል ቢሆንም ባይሆንም የተፈቀደለት አምራች የእያንዳንዱን ወር ሂሳብ የሚቀጥለዉ ወር 30ኛዉ ቀን ከማለፉ በፊት በጸደቀዉ ቅጽ እና በታዘዘዉ አኳሀን ለታክስ ባለስልጣኑ ማስታወቅ እና ከማምረቻ ፋብሪካዉ ወጪ ያደረጋቸዉ እቃዎች ካሉ በዕቃዎቹ ላይ ሊከፈል የሚገባዉን ኤክሳይዝ ታክስ ገቢ ማድረግ አለበት።

## ኤክሳይዝ ታክስን በሚመለከት…

- አስመጪ ወደ ሀገር ውስጥ ባስገባቸው የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ ሊከፍል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ ዕቃዎቹ ወደ ሀገር በገቡበት ጊዜ ለታክሱ ባለሥልጣን መክፈል አለበት፡፡
- የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ ታክሱ የሚሠላው፣የሚከፈለው፣ሂሳቡ የሚያዘው እና የታክሱ ዕዳ በአስገዳጅነት የሚሰበሰበው በጉምሩክ ሕግ መሠረት ይሆናል

**ሙከራ ሁለት**

- ሰነድን የማቅረቢያ ወይም ታክስ የመክፈያ ጊዜ አብራሩ?

# 2.6.1. የፀደቀ ቅጽ

- በታክስ ከፋይ የሚቀርብ ማንኛውም የታክስ ማስታወቂያ፣ ማመልከቻ፣ ማስታወቂያ፣ መግለጫ ወይም ሌላ ሰነድ በፀደቀው ቅጽ መሠረት እንደቀረበ የሚቆጠረው ሰነዱ:-

- የሰነዱ ዓይነት በባለሥልጣኑ በፀደቀ ቅጽ መሠረት የቀረበ፣
- ለማንኛውም ተያያዥ ሰነዶች ጨምሮ ቅጹ የሚጠይቀውን መረጃ የያዘ እና
- ቅጹ በሚጠይቀው መሠረት የተፈረመ ሲሆን ነው።

## 2.6.2. ሰነዶች ለባለሥልጣኑ ስለሚቀርቡበት አኳኋን

- በባለሥልጣኑ በጹሑፍ ካልተፈቀደለት በስተቀር ማንኛውም ታክስ ከፋይ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ የሚጠበቅበትን የታክስ ማስታወቂያ፣ ማመልከቻ፣ መግለጫ ወይም ሌላ ሰነድ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ማቅረብ አለበት። ይህ ድንጋጌ ተፈፃሚ የማይሆንበት ታክስ ከፋይ የታክሰ ማስታወቂያ፣ ማመልከቻ፣ ማስታወቂያ፣ መግለጫ ወይም ሌላ ሰነድ በአካል ወይም መደበኛ ፖስታ በመጠቀም ለባለሥልጣኑ ያቀርባል።

### 2.6.3. ማስታወቂያዎች ስለመስጠት

- ለታክስ ከፋዩ/ለታክስ እንደራሴው/ለታክስ ወኪሉ በአካል በመስጠት/የተላከውን ሰነድ የሚቀበል ሰው ካልተገኘ ማስታወቂያ የንግድ/መኖሪያ ቤት በር በመለጠፍ ማስታወቂያው በትክክል መድረሱን ማረጋገጥ አለበት።

- በእነዚህ ማድረስ ካልተቻለ፣ የህትመት ወጪው በታክስ ከፋዩ የሚሸፈን ሆኖ የፍርድ ቤት ማስታወቂያዎች በሚወጡበት ጋዜጣ ማስታወቂያውን በማውጣት ማስታወቂያ እንዲደርስ ማድረግ ይቻላል።

# 2.6.4. ማስታወቂያዎች....

- በድርጅቱ ማህደር የቅርብ ጊዜ አድራሻ መሠረት የንግድ አድራሻውን ወይም መኖሪያ ቤቱን ማግኘት ካልተቻለ በማህደሩ በተገለጸው ወረዳ ወይም ቀበሌ አስተዳደር በኩል በወረዳው ወይም በቀበሌው ጽ/ቤት በር ላይ እንዲለጠፍ ይደረጋል።
- ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ የታክስ ከፋዩ መደበኛ ወይም በመጨረሻ የሚታወቀው የንግድ ቦታ ወይም መኖሪያ ቤት በሪኮማንዴ ደብዳቤ በመላክ፤

## 2.6.6. የኤሌክትሮኒክ የታክስ ሥርዓት ተግባራዊ ስለማድረግ

- በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ እንዲከናወኑ ሊፈቅዱ የሚችሉ ተግባራት:-

- ለመመዝገብ/ የመለያ ቁጥር ለማግኘት ማመልከቻ ለማቅረብ፣
- የታክስ ማስታወቂያ ወይም ሌላ ሰነድ ለማቅረብ፣
- ታክስ ወይም ሌላ ክፍያ ለመፈፀም፣
- የታክስ ተመላሽ ክፍያ ለመፈፀም፣
- ባለሥልጣኑ የሚያስተላልፈውን ማንኛውንም ሰነድ ለመላክ፣
- በታክስ ሕግ መሠረት መከናወን የሚኖርበትን ወይም እንዲከናወን የተፈቀደ ሌላ ድርጊት ወይም ነገር ለማከናወን።




ዘመናዊ ፈጣን እና ተደራሽነት ያለው ኢንተርኔት በመጠቀም ታክስን የማስታወቅ፣ ክፍያን የመፈፀም፣ ክሊራንስ አገልግሎት የማግኘት እና የታክስ ነክ ጥያቄዎችና ማብራሪያዎች ለማግኘት የሚረዳ አሠራር ከመሆኑም በላይ ግብር ከፋች የራሳቸውን ታክስ ነክ መረጃ በቀላሉ ማንበብ ወይም ማየት የሚችሉበት የኢንተርኔት አሠራር ነው።

## 2.6.7 ኢ-ታክስ የሚያጠቃልላቸው የአገልግሎት ዓይነቶች

- **ኢ-ፋይሊንግ፡-** ግብርን የመላክ/የማሳወቅ
- **ኢ-ፔይመንት፡-** በኢ-ፋይሊንግ የተላከ መረጃ ክፍያ የሚከፍልበት
- **ኢ-ክሊራንስ፡-** የታክስ ምላሽ ክሊራንስ ለመጠየቅ፣ የዓመታዊ ንግድ ፈቃድ ማደሻም ሆነ ሌሎች ክሊራንሶች በኢንተርኔት አገልግሎት የሚገኝበት ነው።
- **የታክስ ነክ መረጃ አገልግሎት፡-** ታክስ ነክ መረጃዎችና ማብራሪያዎች በቀላሉ ማግኘት የሚያስችለው።

**2.6.8. የታክስ ማስታወቂያን በኤሌክትሮኒክስ ማቅረብ ያለው ጠቀሜታ**

- 24/7 ወይም 365 ቀን ግብርን ማስታወቅ ያስችላል።
- አላስፈላጊ የጊዜ፣ የሰው ሃይል እና የገንዘብ ወጭዎች ይቀንሳል።
- የሚሰወሩና የሚጠፉ ሰነዶችን በቀላል መንገድ መቆጣጠር ያስችላል፤
- አደጋን/የገንዘብ መጥፋትን ይቀንሳል።

**ሙከራ ሶስት**

- ታክስን በኤሌክትሮኒክስ የታክስ ሥርዓት መጠቀም ያለውን ጥቅም አብራሩ?

# 2.6.9. ማስታወቂያን ተቀባይነት የማያሳጣ ጉድለት

- ማስታወቂያን ተቀባይነት የማያሳጣ ጉድለት ተፈፃሚ የሚሆነው:-

- የተሰጠው ማስታወቂያ የታክስ ሕግ ዓላማ እና መንፈስ ጋር የሚስማማ ወይም የተጣጣመ ከሆነ፤ እና
- በማስታወቂያው የተለየው የጋራ ዓላማን እና ግንዛቤን መሠረት አድርጎ ከሆነ ነው።

# ማስታወቂያን ተቀባይነት የማያሳጣ ጉድለት...

- ማስታወቂያን ተቀባይነት የማያሳጣ ጉድለት ተፈፃሚ በሚሆንበት ጊዜ:-

  - ለማስታወቂያው መሠረት የሆነው የታክስ ሕግ ማንኛውም ድንጋጌ አልተጠበቀም በሚል ምክንያት ማስታወቂያውን ተቀባይነት ማሳጣት፤

  - የታክስ ስሌት ማስታወቂያው ወይም ማንኛውም ሌላ ሰነድ ፎርም አልተሟላም በሚል ውድቅ ማድረግ ወይም እንዳልተሰጠ መቁጠር ወይም እንዳልተሰጠ እንዲቆጠር ማድረግ እና

  - በታክስ ስሌት ማስታወቂያው/ ሌላ ሰነድ ላይ በሚታይ ስህተት፣ ግድፈት/ጉድለት ምክንያት ተቀባይነት ማሳጣት አይቻልም።

# ማስታወቂያን ተቀባይነት የማያሳጣ ጉድለት…

- ❑ ስህተቱ ወይም ልዩነቱ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ የተሰጠውን ታክስ ከፋይ የሚያሳስት እስካልሆነ ድረስ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ለሚከተሉት ምክንያቶች ዋጋ ሊያሳጣ አይችልም:-

- ➢ በታክስ ስሌት ማስታወቂያው በተጠቀሰው የታክስ ከፋይ ስም፣ በተገለፀው የገቢ ወይም የገንዘብ መጠን ወይም እንዲከፈል በተጠየቀው የታክስ መጠን ስህተት ምክንያት፣
- ➢ በተዘጋጀው የታክስ ስሌት እና ለታክስ ከፋዩ በተሰጠው የታክስ ስሌት ማስታወቂያ መካከል በሚታይ ልዩነት ምክንያት።

# ማስታወቂያን ተቀባይነት የማያሳጣ ጉድለት...

- ስህተቱ ወይም ልዩነቱ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ የተሰጠውን ታክስ ከፋይ የሚያሳስት እስካልሆነ ድረስ የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ለሚከተሉት ምክንያቶች ዋጋ ሊያሳጣ አይችልም:-

- በታክስ ስሌት ማስታወቂያው በተጠቀሰው የታክስ ከፋይ ስም፣ በተገለፀው የገቢ ወይም የገንዘብ መጠን ወይም እንዲከፈል በተጠየቀው የታክስ መጠን ስህተት ምክንያት፣
- በተዘጋጀው የታክስ ስሌት እና ለታክስ ከፋዩ በተሰጠው የታክስ ስሌት ማስታወቂያ መካከል በሚታይ ልዩነት ምክንያት።

## 2.7. የታክስ ማስታወቂያ ዘግይቶ ማቅረብ አስተዳደራዊ ቅጣት

- የታክስ ማስታወቂያ ግዴታውን ያልተወጣ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ የታክስ ጊዜ ያልተከፈለውን ታክስ 5%፤ 25% እስኪሞላ ድረስ ይቀጣል፤
- ለመጀመሪያው የሒሣብ ጊዜ የታክስ ማስታወቂያ ያላቀረበ ሰው ቅጣት ከብር 50ሺ አይበልጥም፡፡
- በማንኛውም ሁኔታ የሚጣለው ቅጣት ቀጥሎ ከተመለከቱት ከዝቅተኛው ያነሰ አይሆንም፤

I . ብር 10,000 (አስር ሺህ ብር)፣

# አስተዳደራዊ ቅጣት…

||. በታክስ ማስታወቂያ ላይ መመልከት ከነበረበት የታክስ መጠን መቶ በመቶ።

- ታክስ ከፋዩ በታክስ ጊዜው ሊከፍል የሚገባው ታክስ የሌለው እንደሆነ የታክስ ማስታወቂያ ሳያቀርብ ለዘገበት ለእያንዳንዱ የታክስ ጊዜ 10 ሺህ ብር ቅጣት ይከፍላል።

## ሙከራ አራት

- ታክስን ባላማሳወቅ የሚያስከትለው ቅጣት አብራሩ?

- ማንኛውም መንግሥት ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት የሚያስፈልገውን ወጪ ለመሸፈን ታክስን በሕግ ይጥላል፤ ይሰበስባል፡፡
- በታክስ ሥርዓቱ ውስጥ ያሉ ግብር ከፋዮችም፤ ታክስን በወቅቱ ማሳወቅ የሀገራችን ህልውና ነው፡፡ ግብርን በወቅቱ ለማሳወቅ የቀረቡትን የታክስ ማስታወቂያዎች እና ቅጾች መረጃ በተግባር ላይ ማዋል ጠቀሜታቸው የጎላ ነው፡፡

## ማጣቀሻ

- የፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 እና ደንብ ቁጥር 410/2009
- የፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 እና ደንብ ቁጥር 407/2008
- የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁትር 285/1994፤ አዋጁን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 609/2008 እና ቁጥር 1157/2011
- የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 308/1995 እና ማሻሻው ቁጥር 611/2001
- የኤክሳይ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012
- Federal Democratic Republic of Ethiopia Federal Tax Administration Proclamation No. 983/2016 Technical Notes

.

# አመሰግናለሁ